# ምክር ቤቱ በቆሼ ለደረሰው አደጋ የገንዘብ እና የቁሳቁስ ድጋፍ አደረ

የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት፣ የምክር ቤቱ የቦርድ አባላትና ሠራተኞች ቅዳሜ መጋቢት 2 ቀን 2009 ዓ.ም. በመዲናችን በተለምዶ ‹ቆሼ› ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በቆሻሻ ክምር መደርመስ ሳቢያ ቤት ንብረታቸው ለወደመባቸውና ከቀዬአቸው ተፈናቅለው በጊዜያዊ መጠለያ ውስጥ ለተጠለሉ የአደጋው ሰለባዎች መጋቢት 9 ቀን 2009 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ከንቲባ ጽ/ቤት በመገኘት የ174ሺ. ብር የገንዘብ ርዳታ አደረጉ፤ በኮ/ቀራንዮ ወረዳ 1 ወጣት ማዕከል ጊዜያዊ መጠለያም በመገኘት የተለያዩ የጫማና የአልባሳት ርዳታም ተበርክቷል፡፡

የምክር ቤቱ ፕሬዚደንት አቶ ሰለሞን አፈወርቅ እንደተናገሩት ም/ቤቱ፣ የምክር ቤቱ የቦርድ አባላትና ሠራተኞች ያደረጉት ድጋፍ በቂ ሳይሆን ችግሩን በጊዜያነት ለመፍታት የተደረገ ድጋፍ መሆኑን ገልጸው፣ ለወገን ደራሽ ወገን ነውና ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት የንግዱ ማኅበረሰብም መጠጊያና መሸሸጊያ ላጡት የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲሁም ያለጧሪ ለቀሩት እናቶችና አረጋውያን የአደጋው ሰለባዎች የገንዘብና የቁሳቁስ ርዳታ እንደሚያደርግ እምነታቸውን ገልጸዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አቶ ድሪባ ኩማ በበኩላቸው፤ ለተደረገው ድጋፍ አመስግነው በህይወት የተረፉትን ለማቋቋም የግሉ ዘርፍ በገንዘብም ሆነ በቁሳቁስ የሚያደርገውን ድጋፍ እንደሚቀጥል ያላቸውን እምነት የገለጹ ሲሆን የከንቲባው ጽ/ቤትም በበኩሉ እነዚህን ወገኖች በተገኘው ድጋፍ በዘላቂነት ለማቋቋም አስፈላጊውን ሁሉ እንሚያደርግ ተናግረዋል፡፡

በመጨረሻ ምክር ቤቱ ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉት የሟች ቤተሰቦችና የሐዘኑ ቁስል ለገረፋቸው ወገኖች መጽናናትን ይመኛል፡፡

የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የግሉን ዘርፍ መብትና ጥቅም በማስከበር ዘርፉ በሀገር ኢኮኖሚ ውስጥ የመሪነት ሚና እንዲጫወት በአዋጅ የተቋቋመ ተቋም መሆኑ ይታወቃል፡፡